# ትንቢተ አብድዩ

## መግቢያ

### ጸሐፊው

ይህን መጽሐፍ የጻፈው አብድዩ ሲሆን፣ የስሙ ትርጉም "የእግዚአብሔር አገልጋይ" ማለት ነው:: "አብድዩ" የሚለው ስም በዚያን ጊዜ የተለመደ ስም ነበር (1ነገ 18፥3-16፤ 1ዜና 3፥21፤ 7፥3፤ 8፥38፤ 9፥16፤ 12፥9፤ 27፥19፤ 2ዜና 17፥7፤ 34፥12፤ ዕዝ8፥9፤ ነህ10፥5፤ 12፥25 ይመ):: የአባቱም ስም ሆነ የትውልድ ቦታው የት እንደ ሆነ አልተገለጸም::

### የተጻፈበት ጊዜና ቦታ

የተጻፈበትን ጊዜና ቦታ ለይቶ የማወቁ ጉዳይ አከራካሪ (አነጋጋሪ) ነው:: ትንቢቱ የተጻፈበትን ጊዜ ለማወቅ በቊ11-14 ላይ የተጻፈውን ሐሳብ፣ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ጉልሕ ስፍራ ካላቸው ቀጥሎ ከተጠቀሱት ሁለት ድርጊቶች ከአንዱ ጋር ማገናዘብ ያስፈልጋል::

1. በኢዮራም ዘመነ መንግሥት ፍልስጥኤማውያንና ዐረቦች በኢየሩሳሌም ላይ ያደረጉት ወረራ (853-841 ዓ.ቅ.ክ.)፤ 2ነገ 8፥20-22፤2ዜና21፥8-20 ይመ:: ከዚህ አንጻር ሲታይ አብድዩ ኤልሳዕ በነበረበት ዘመን ነበር ማለት ነው::

2. ባቢሎናውያን በኢየሩሳሌም ላይ ያደረጉት ወረራ (605-586 ዓ.ቅ.ክ)፤ ይህ ከሆነ አብድዩ ኤርምያስ በነበረበት ዘመን ነበረ:: ይኸኛው አማራጭ የበለጠ አሳማኝ ይመስላል:: በአብ ከቁ1-9 እና በኤር49፥7-22 መካከል ያለው መመሳሰል፣ ብዙ ሰዎች በአብድዩና በኤርምያስ መጽሐፍ መካከል አንድ ዐይነት መደጋገፍ አለ ብለው ለመናገር ምክንያት ሆኖአቸዋል፤ ሆኖም ሁለቱም ነቢያት ለኛ ካልታወቀ ከአንድ የጋራ ምንጭ በመቅዳት ጽፈውም ሊሆን ይችላል::

### የመጽሐፉ ወጥነትና መሪ ሐሳቡ

የዚህን አጭር ትንቢት ወጥነት በሚመለከት እንድንጠራጠር የሚያደርገን የጐላ ምክንያት የለም:: የመጽሐፉ መሪ ሐሳብ፣ በነበራት ጸጥታና ሰላም የታበየችው ኤዶም እስራኤል በባዕዳን ኀይል በመ ጥፋቷ ደስ መሰኘቷን የሚያመለክት ነው:: ስለዚህ ኤዶም በዚህ ሁኔታ በእስራኤል መጥፋት ተባባሪ በመሆንዋ፣ የእግዚአብሔር ቊጣ በላይዋ ይመጣል፤ እርሷ ራሷ ትጠፋለች፤ ነገር ግን የጽዮን ተራራና እስራኤል ከጥፋት ይድናሉ፤ የእግዚአብሔርም መንግሥት ድል ያደርጋል::

ኤዶም በእስራኤል ላይ የፈጸመችው የጠላትነት ድርጊት የእስራኤልን ዕድሜ አራዝሞታል:: በእስራኤልና በኤዶም መካከል ያለውን ግንኙነት ለመገንዘብ ቀጥሎ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃዎች መመልከቱ ጠቃሚ ነው:: ዘፍ27፥41-45፤ 32፥1-21፡33፡36፤ ዘፀ15፥15፤ ዘኁ20፥14-21፤ ዘዳ2፥1-6፤23፥7፤ 1ሳሙ22ን ከመዝ52ጋር፤ 2ሳሙ8፥13-14፤ 2ነገ8፥20-22፤ 14፥7፤ መዝ83፤ ሕዝ35፤ ኢዮ3፥18-19፤ አሞ1፥1-12፤ 9፥1::)

ኤዶማውያን ከእስራኤላውያን ጋር የተዛመዱ ስለሆኑ (ቊ10) በጠላትነት መቆማቸው በእጅጉ የሚያስ ወቅሳቸው ነው:: ኤዶም እስራኤልን ለመርዳት ወደ ኋላ ማለትዋና ያሳየችው ግልጽ ተቃውሞ ሙሉ በሙሉ የሚያስጠይቃት ነው:: እግዚአብሔር ዔሳውን (መጥላቱ) (ዘፍ 25፥23፤ ሚል1፥3፤ ሮሜ9፥13) በምንም መንገድ ኤዶማውያንን ነጻ ሊያደርጋቸው አይችልም:: ኤዶም በተራራ ላይ ባሉት ምሽጎችዋ የተመካች ቢሆንም፣ ከዚያ ትወርዳለች፤ ትበዘበዛለችም:: እስራኤል ግን እግዚአብሔር ከእርስዋ ጋር በመሆኑ ብልጽግናዋ ይበዛል::

### አስተዋፅኦ

1 ርእስና መግቢያ (1)

2 በኤዶም ላይ የተነገረ ፍርድ (2-14)

- ሀ. ኤዶም እንደምትጠፋ መገለጹ (2-7)
  1. መዋረዷ (2-4)
  2. ፍጹም መደምሰሷ (5-7)
- ለ. የኤዶም መጥፋት እርግጠኛነት (8-14)
  1. ኀፍረቷና ጥፋቷ (8-10)
  2. በእስራኤል ላይ የፈጸመችው በደል (11-14)

3 የጌታ ቀን (15-21)

- ሀ. ፍርድ በአሕዛብ ላይ፣ ትድግና ግን ለጽዮን (15-18)
- ለ. የእግዚአብሔር መንግሥት መመሥረት (19-21)

